# የአቶ ታዬ ጉልላት አጭር የሕይወት ታሪክ

አቶ ታዬ ጉልላት ከአባቱ ከደጃዝማች ጉልላት ታዬና ከእናቱ ከወ/ሮ ንጋቷ ኃይሌ በአዲስ አበባ ከተማ ተወለደ፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን በተስፋ ኮከብ፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በልዑል መኮንን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ቀጥሎም የዩኒቨርስቲ ትምህረቱን በዩኒቨርስቲ ኦፍ ካሊፎርኒያ፣ ዴቪስ አጠናቋል፡፡

ከ1966 ዓ.ም. አብዮት በኋላ ለዲሞክራሲና ለፍትህ የሚደረገውን ትግል የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ /ኢህአፓ/ ወጣት ክንፍ አባል በመሆን የተቀላቀለ ሲሆን በመጀመሪያ በአዲስ አበባ ከተማና በአካባቢው በነበረውትግል ውስጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ከዚያም የኢህአፓ ሠራዊት አባል በመሆን በትግራይ፥በቤጌምድርና በሰሜን ክፍለ ሃገሮች ውስጥ ሠራዊቱ በመደበው ቦታ ሁሉ በጽናትና በጀግንነት የታገለ ወንድማችን ነበር፡፡

በወቅቱ ለህክምና ትምህርት ወደ ቻይና ተልኮ በአኩፓንቸርና በጠቅላላ የህክምና ሙያ ተጨማሪ ትምህርት ተምሮ ወደ ሜዳ ተመልሷል፡፡ ከዚያም ከሌሎች የድርጅቱ አባላት ጋር በስደት ወደ አሜሪካ በመምጣት ቀደም ሲል ጀምሮት የነበረውን ትግል ቀጥሎ ሕይወቱ እስከ አለፈበት ቀን ድረስ በተለያየ ደረጃ ትግሉን ይጠቅማል ባለበት ሁሉ በንቃት ሲሳተፍ ቆይቷል፡፡

ወንድማችን ታዬ /ጳውሎስ/ ጀግንነትን፣ ፍቅርን፣ ትህትናን፣ጽናትን አጣምሮ የያዘ ታላቅ ኢትዮጵያዊ ነበር፡፡

በተለያዩ የአሜሪካ ግዛቶች በአኩፓንቸርና በሌላም የሕክምና አገልግሎት ሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም በእነዚህ አካባቢ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እንደሚያውቁት የነጻ አኩፓንቸር ዕርዳታና የሕክምና አገልግሎት እየሰጠ ከተለያዩ የነርቭ በሽታዎች እንዲድኑ አድርጓል፡፡

የእኛ ታዬ የጓደኞቹ ደግሞ ጳውሎስ ሳይተርፈው የሚሰጥ፣ ሳይበላ የሚያጎርስ፣ ሕይወቱን በሙሉ ለሌሎች በጎ በመሥራት የኖረ ነበር ስለዚህ ምንም እንኳን ለእኛ በሥጋ ቢወለደንም ጳውሎስ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ወንድም በመሆኑ ኃዘኑ የሁላችንም መሆኑ ይታወቃል፡፡

የሰው መለያው በሕይወት እያለ ያከናወነው ተግባሩ ነው፡፡ የጳውሎስን የወገንና የሃገር ፍቅር፣ ቆራጥነትና ጽናት ለምናውቅ ሁሉ ወንድማችን በአካልም ሆነ በመንፈስ የኢትዮጵያዊነት መገለጫ ነበር ማለት ይቻላል፡፡

ዛሬ ጳውሎስ ከመካከላችን በሞት በመለየቱ ኃዘናችን የመረረ ቢሆንም ከጓደኞቹና ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር የምንጋራው መሆኑ እንድንጽናና ያደርገናል፡፡

ከተለያዩ የአሜሪካ ግዛቶችና ከካናዳ በአካል በመገኘት የኃዘናችን ተካፋይ ከመሆናችሁም በላይ ውድ ጊዜያችሁን መስዋዕት በማድረግ፥በገንዘብ፥በጉልበትና በሃሳብ ለረዳችሁን ሁሉ እንዲሁ በአካል በመገኘት ያልተለያችሁን፣ በተለያየ የዓለም ክፍሎች ሆናችሁ በስልክ፣ በደብዳቤ፣ እንዲሁም በኢሜል የኃዘናችን ተካፋይ በመሆን እንድንጽናና ያበረታታችሁን ሁሉ ከልብ የመነጨ ምስጋናችን በልጆቹና በልጅ ልጆቹ እንዲሁም በቤተ ሰቡና በጓደኞቹ ስም እናቀርባለን፡፡

አምላክ ሁላችንንም ብርታቱን እንዲሰጠን እንለምናለን!!!

ቤተሰቦቹ
ወ/ሮ ምህረት ታዬ ጉልላት
ወ/ት ያበሻወርቅ ግርማ
አቶ ሽመልስ ጉልላትና ቤተሰቡ
ወ/ሮ አስስናቀች ጉልላት
ወ/ት ማሪያምማዊት ይርሳልኝ







## የአቶ ታዬ ጉልላት የቀብር ሥነ ስርዓት እና ፍትሃት/Wake/

| | |
|---|---|
| ቀን/ Date | Oct 11, 2014 |
| ሰዓት / Time | 9:00 – 12:00 |

አድራሻ/ Address St. James Armenian Apostolic Church
465 Mount Auburn St.
Watertown, MA 02472

### ቀብር ስነስርዓት / **Burial Ceremony/**

| | |
|---|---|
| ቀን/ Time | 12:00 – 1:30 |
| ሰዓት / Address | Cambridge Cemetery<br>76 Coolidge Avenue<br>Cambridge, MA 02138 |

**ማስታወሻ -ከቀብሩ ሥነ ሥርዓት በኋላ ጸበል ጸዲቅ**

**በ** St. James Armenian Apostolic Church
465 Mount Auburn St.
Watertown, MA 02472 **ይከናወናል::**

# አቶ ታዬ ጉልላት
# /ጳውሎስ/



## ጳውሎስ ልጠይቅህ

በእናትህ ጨክነህ በአባትህ ጨክነህ ከቤት የወጣኸው፥
አገሬን ላድናት ብለህ የፎከርከው፥
እንደ ሆ ቺሚን እንደ ቼጉቬራ ፋኖ ተሰማራ ብለህ የዘመርከው፥
ደርግን ከነትጥቁ መላ ያሳጣኸው፥
አገር ልታለማ ገጠር የገባኸው፥ ያሲንባን በረሃ ወጥተህ የወረድከው፥
የወያኔን ሴራ ቀድመህ በመረዳት ሱዳን የገባኸው፥
ለጥገኝነቱ የተለማመጥከው፥
ጳውሎስ ልጠይቅህ ልፋትህ ለዚህ ነው?

ጥይት ያልደፈረው ጠንካራ ልብህ፥ በመቀስ ተረታ ታየ ስንፍናህ፥
ሃገር እንድትመራ ተስፋ የጣልኩብህ፥
ወገን እንድታድን ተስፋ የጣልኩብህ፥
ምነው ጉድ አረከኝ በሰው አገር ቀረህ።

ያልታደለች አገር ሰው የማይወጣባት፥
ደህናዎቹ ሲያልቁ እንዳሻቸው ያርጓት።

ውሳኔ ለመስማት ታንጋጥጥ ነበረ፥ በስተመጨረሻው ዓይንህ ተከደነ፥
ቆርጠህ ከተነሳህ ለመሄድ ወስነህ፥ ማንን ተካህበት ለጅምሩ ሃሳብህ?

መዋተት መልፋትህ ለሃገር ነበረ፥ መዋትህ መልፋትህ ለወገን ነበረ፥
መስከረም 23 ሁሉ ነገር ቀረ።

ረሃቡን ጥሙን ሁሉንም አይተሃል፥ አግኝተህ ለመርዳት ቀዳሚ ሆነሃል፥
ነለሁህ የሚሉህ ጓደኛ አፍርተሃል፥ አረፍ በል ይበቃል ከፉኛ ደክመሃል።

ደብቆ መስጠትን የለመደው እጅህ፥
ለሰው መራራትን የሚያውቀው አዕምሮህ፥
መሳቅ መጫወት ነው ዘወትር ልማድህ፥
ማን አስቀይሞህ ነው ድንገት ዝም ማለትህ?

አልናፈቀህም ወይ ከሴ ዳማከሴው የጦስኙ ሽታ?
እሰው አገር ስትቀር በአንድ ቀን በሽታ።

የተስተካከለው የአገርህ ዓየር፥
ያድንህ ነበረ ወደዚያ ብትበር።

ሁሉም አለሆነልህ እንደወጣህ ቀረህ፥
እንዴት የሚያስብ ይስጣት ለሃገርህ።

## ጳውሎስ ልጠይቅህ

በእናትህ ጨክነህ በአባትህ ጨክነህ ከቤት የወጣኸው፥
አገሬን ላድናት ብለህ የፎከርከው፥
እንደ ሆ ቺሚን እንደ ቼጉቬራ ፋኖ ተሰማራ ብለህ የዘመርከው፥
ደርግን ከነትጥቁ መላ ያሳጣኸው፥
አገር ልታለማ ገጠር የገባኸው፥ ያሲንባን በረሃ ወጥተህ የወረድከው፥
የወያኔን ሴራ ቀድመህ በመረዳት ሱዳን የገባኸው፥
ለጥገኝነቱ የተለማመጥከው፥
ጳውሎስ ልጠይቅህ ልፋትህ ለዚህ ነው?

ጥይት ያልደፈረው ጠንካራ ልብህ፥ በመቀስ ተረታ ታየ ስንፍናህ፥
ሃገር እንድትመራ ተስፋ የጣልኩብህ፥
ወገን እንድታድን ተስፋ የጣልኩብህ፥
ምነው ጉድ አረከኝ በሰው አገር ቀረህ::

ያልታደለች አገር ሰው የማይወጣባት፥
ደህናዎቹ ሲያልቁ እንዳሻቸው ያርጓት::

ውሳኔ ለመስማት ታንጋጥጥ ነበረ፥ በስተመጨረሻው ዓይንህ ተከደነ፥
ቆርጠህ ከተነሳህ ለመሄድ ወስነህ፥ ማንን ተካህበት ለጅምሩ ሃሳብህ?

መዋተት መልፋትህ ለሃገር ነበረ፥ መዋትህ መልፋትህ ለወገን ነበረ፥
መስከረም 23 ሁሉ ነገር ቀረ::

ረሃቡን ጥሙን ሁሉንም አይተሃል፥ አግኝተህ ለመርዳት ቀዳሚ ሆነሃል፥
ለሁህ የሚሉህ ጓደኛ አፍርተሃል፥ አረፍ በል ይበቃል ከፉኛ ደክመሃል::

ደብቆ መስጠትን የለመደው እጅህ፥
ለሰው መራራትን የሚያውቀው አዕምሮህ፥
መሳቅ መጫወት ነው ዘወትር ልማድህ፥
ማን አስቀይሞህ ነው ድንገት ዝም ማለትህ?

አልናፈቀህም ወይ ከሴ ዳማከሴው የጠስኙ ሽታ?
እሰው አገር ስትቀር በአንድ ቀን በሽታ::

የተስተካከለው የአገርህ ዓየር፥
ያድንህ ነበረ ወደዚያ ብትበር::

ሁሉም አለሆነልህ እንደወጣህ ቀረህ፥
እንዳተ የሚያስብ ይስጣት ለሃገርህ::

ከዚህ ዓለም በሕምም ምክንያት የተለየው

የወንድማችን የታዬ / ጳውሎስ/

የቀብር ሥነ ሥርዓት

ፕሮግራም ቅደም ተከተል - ቅዳሜ ኦክቶበር 11 ቀን 2014 ዓ.ም.

1. የጸሎትና የቡራኬ ሥነ ሥርዓት - በቦስተን የመካነ ሕይወት ቅ/ሚካኤል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤ/ክ 9:00 – 11am

2. የታዬ / ጳውሎስ/ አጭር የሕይወት ታሪክ ከቤተሰብ ወ/ት ማሪማዊት ይርሳልኝ 11:00 – 11: 10am

3. የግል ትውስታ
   - ከቅርብ ወዳጆቹ
     ፊሊጶስ አርቲን 11:10 -11: 20am
   - ግጥም ከቤተሰብ
     ወ/ሮ ሙሉነሽ አበባየሁ 11: 20 -11:35am
   - ግጥም ከጓደኞቹ
     11:35 -11:45am

4. አሁን የመጨረሻውን ስንበት አድርገን በመከታተል ወደ ቀብር ስፍራ ማለት ወደ 11:45 -12:00pm
   Cambridge Cemetery
   76 Coolidge Avenue
   Cambridge, MA 02138 እናመራለን

<u>ማስታወሻ</u> - ከቀብሩ ሥነ ሥርዓት በኋላ ጸበል ጸዲቅ
በ St. James Armenian Apostolic Church
465 Mount Auburn Street
Watertown, MA 02472 ይከናወናል::

እግዚአብሔር ቤተሰቡን ከዳግማዊ ሀዘን ይሰውርልን!!!